**ETHIOPIA**

## የአጠቃቀም መመሪያ

**ትክክለኛውን ውጤት ለማወቅ የአጠቃቀም መመርያውን በጥንቃቄ መከተል ያስፈልጋል። ምርመራውን ከማድረጎት በፊት ባሉት 15 ደቂቃዎች ውስጥ መመገብ እና መጠጣት ወይም ከ30 ደቂቃዎች በፊት ማንኛውንም የአፍ ንጽህና መጠበቂያ ኬሚካሎችን መጠቀም ክልክል ነው፡፡**


**ማስጠንቀቂያ: የፀረ ኤችአይቪ ህክምና (ART) ላይ ከሆኑ የሚያገኙት የምርመራ ውጤት የተሳሳተ ሊሆን ይችላል፡፡**

መመርያዎችን ይመልከቱ

www.oraquickhivselftest.com

ORAQUICK® HIV SELF-TEST

## የኦራ ኪዩክ ኤችአይቪ እራስን በራስ መመርመሪያ አጠቃቀም




**ምርመራው የሚፈጀውን ጊዜ ለመቁጠር የሚያስችል ሰአት ያስፈልገናል፡፡**




የመመርመሪያ እሽጉ የሚይዘው: የመመርመሪያ መሳሪያ እሽግ :የመመርመሪያ ብልቃጥ ማስቀመጫ እና የምርመራው መመሪያ ናቸው፡፡




የመመርመሪያ መሳሪያው እሽግ በውስጡ ሁለት እሽጎች አሉት፡፡




ብልቃጡ የያዘውን እሽግ በመቅደድ ይክፈቱ




ብልቃጡን ይክፈቱ





ፈሳሹን እንዳያፈሱት፡፡ እንዳይጠጡት፡፡




ብልቃጡን በማስቀመጫው ላይ ጋደል አድርገው ያስቀምጡ





የመመርመሪያ ዘንጉን የያዘውን እሽግ በመቅደድ ከፍተው ዘንጉን ያውጡ፡፡ የዘንጉ ጠፍጣፋ ጫፍ በእጅ መነካት የለበትም፡፡ እሽጉ እንዳይበላሽ የሚያደርግውን ማቆያ መብላት/መዋጥ የተከለከለ ነው፡፡




የመመርመሪያ ዘንጉን ጫፍ ጫን አድርገው በመያዝ በመጀመሪያ የላይኛውን (ምስል 1) በመቀጠል የታችኛውን (ምስል 2) ድድ አንድ ጊዜ ብቻይጥረጉ::




የመመርመሪያ ዘንጉን ጠፍጣፋ ጫፍ ሙሉ ክፍል የብልቃጡን ወለል እስኪነካ ድረስ ወደ ውስጥ በማስገባት ያቆዩ፡፡




**ለ20 ደቂቃ ይጠብቁ ፡፡ ከ20 ደቂቃ በኋላ ውጤቱን ያንብቡ ፡፡ውጤቱ 40 ደቂቃ ሳያልፈው መነበብ አለበት፡፡ ውጤቱ 40 ደቂቃ ካለፈው ዋጋ አይኖረውም፡፡**

## የውጤት ንባብ — የሙከራ ውጤቶችን ጥሩ ብርሃን ባለው አካባቢ ያንብቡ

### ኤችአይቪ በደሞ ውስጥ መኖሩን የሚያሳይ ውጤት




ሁለት መስመሮች ካሉ መስመሩ ደብዛዛ ቢሆንም እንኳን ውጤቱ ኤችአይ ቪ በደሞት ውስጥ አለ ማለት ሊሆን ስለሚችል ተጨማር ምርመራ ማድረግ አለብዎት።

→ **ወዲያውኑ አቅራቢያዎ ወደሚገኝ ጤና ተቋም መሄድ ይኖርብዎታል።**

### ከኤችአይቪ ነፃ ውጤት

**ከ20 ደቂቃ በፊት ውጤቱን ማንበብ ትክክለኛ ውጤትን ላይነግረን ይችላል**




‘C’ አጠገብ አንድ መስመር ካለ እና ከ ‘T’ አጠገብ ምንም መስመር ከሌለ ውጤቱ ከኤችአይቪ ነፃ ማለት ነው፡፡

→ ለኤችአይቪ ተጋላጭነት ካለዎት በየሦስት ወሩ መመርመር ይኖርቦታል፡፡

### ትክክል ያልሆነ ውጤት




ከ ‘C’ አጠገብ ምንም መስመር ከሌለ (ከ ‘T’ አጠገብ መስመር ቢኖርም እንኳን) ወይም የመመርመሪያ ዘንጉ ለማንበብ አዳጋች/አስቸጋሪ ከሆነና በቀይ ደም ከተሸፈነ የምርመራው ሂደት በትክክል አልሰራም ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ምርመራው በድጋሚ መሰራት ይኖርበታል፡፡

**ምርመራውን ለመድገም ሌላ አዲስ እሽግ መጠቀም ይኖርቦታል፡፡**

→ **ምርመራው በትክክል ካልሰራ ወደ አቅራቢያዎ የሚገኝ**

**ጤና ተቋም በመሄድ በድጋሚ ምርመራ ያድርጉ፡፡**

### ስለ ውጤቱ እርግጠኛ አለመሆን

ውጤትዎን ካላወቁ ወይም ስለ ውጤቱ እርግጠኛ ካልሆኑ

→ ጤና ተቋም በመሄድ በድጋሚ ምርመራ ያድርጉ፡፡

### አወጋገድ

የመመርመሪያ ዘንጉን ከብልቃጡ በማወጣት ብልቃጡን መክደኖንና ሁሉንም ነገሮች ወደ ቆሻሻ መጣልዎን እንዳይዘነጉ፡፡

## የምርት መረጃ

**REF** 5X4-1000, 5X4-1001, 5X4-2001

**ከUSA ውጭ ብቻ ለጥቅም የሚውል**
**ለአንድ ጊዜ ምርመራ ብቻ የሚያገለግል!**

### የምርቱ ጠቀሜታ

OraQuick® ኤች.አይ.ቪን በአፍ ፈሳሽ አማካኝነት ራስን በራስ በመመርመር የኤችአይቪ -1 እና ኤች.አይ.ቪ-2 ጸረ ተዋህሳያን እንዳለ ለማወቅ ጥቅም ላይ የሚውል የምርመራ ዘዴ ነው። ይህ ምርመራ በበሽታው ከተያዙ ግለሰቦች የኤችአይቪ-1 እና ኤችአይቪ-2 ጸረ ተዋህሳያን ለመለየት እንዲረዳ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።


### የምርመራው አጭር ገለፃ

ይህ OraQuick® የኤችአይቪ ራስን በራስ መመርመርመሪያ ዘዴ፣ በአፍ ውስጥ የሚገኙ ፈሳሾችን በመጠቀም የሰው የበሽታ መከላከያ ስርዓት የሚያዳክም ቫይረስ አይነት 1 (ኤችአይቪ-1) እና አይነት 2 (ኤችአይቪ-2) ጸረ ተዋህሳያን አካላትን ለመለየት ለአንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ ይውላል። ይህ OraQuick® ኤችአይቪ ራስን በራስ መመርመርያ በህክምና ዘርፍ ላልተሰማሩ ተጠቃሚዎች በራሳቸው የኤችአይቪ ምርመራ በቀላሉ እንዲያከናውኑ ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ምርመራው የመመርመሪያ መሳሪያውን ጠፍጣፋ አካል ወደ አፎ ውስጥ በመክተት ይከናወናል፤ ስለዚህ የጠፍጣፋው የመሳሪያ አካል በአፎና በውጫዊው ድድ መካከል ይሆናል፤ ከዚያም በውጭ ባለው የድድ መስመር በኩል አንድ ጊዜ ይጠርጋሉ። መመርመሪያው ተመጥኖ ወደ ተዘጋጀ ፈሳሽ ያለው ብልቃጥ ውስጥ ይቀመጣል። ከድዱ ላይ የመጣ ፈሳሽ በንጣፉ ጠፍጣፋው በኩል ወደ መሳርያው ይፈሳል፤ ከዛ ወደ ምርመራ ድርድር የቀጥላል። የኤችአይቪ ቫይረስ ከተገኘ በዉጤት መስጫው ዉስጥ በ 'T' አጠገብ ቀለም ያለው መስመር ይወጣል። ምንም የኤችአይቪ ጸረ ተዋሳህያን አካላት ካልተገኙ፣ በዚያ አካባቢ ምንም የመስመር ቅርጾች አይገኙም። ምርመራው በትክክል ከተከናወነ፣ በውጤቱ መስኮት በ 'C' አካባቢ የመስመር ቅርጽ ይሰራል። ይህ የቁጥጥር መስመር ይባላል።

### የምርመራ አፈጻጸም

ጥናቶች እንደሚያሳዩት በደማቸው ውስጥ ኤችአይቪ ቫይረስ ይኑርባቸው አይኑርባቸው የማያውቁ 900 ሰዎች ኤችአይቪን ራስን በራስ መመርመርያ OraQuick® እራሳቸውን በራሳቸው እንዲመረምሩ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ውጤቱም በላቦራቶሪ ውስጥ ከሚገኝ የ4ተኛ ትውልድ የኤች አይ ቪ መመርመሪያ ጋር እንዲነፃፀሩ ተደርጓል፡፡ የላብራቶሪ ውጤቱ እንደሚያሳየው 153 ሰዎች ኤችአይቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ የተገኘ ሲሆን 724 የሚሆኑት ደግሞ አልተገኘባቸውም፡፡ ሰባት (7) ሰዎች ከጥናቱ እንዲወጡ ተደርጓል፡፡ የውጤቶቹ ንጽጽር ከዚህ እንደሚከተለው ነው፥

- 99.4% የሚሆኑት ሰዎች (ከ153 ውስጥ 152) ውጤታቸው ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ እንዳለ በትክክል ገልፀዋል፡፡ ይህ ማለት ከ153 ሰዎች ውስጥ 1 ሰው ኤችአይቪ ቫይረስ በደሙ ውስጥ እያለ የለም ብሎ ገልጻል፡፡ ይህ የውሸት ኤችአይቪ በደሜ ውስጥ የለም ይባላል፡፡
- 99.0% የሚሆኑት ሰዎች ማለትም ከ (717/724) ውጤታቸው ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ እንደሌለ በትክክል ገልፀዋል፡፡ ይህም ማለት ከ724 ሰዎች ውስጥ 7 ሰዎች ኤችአይቪ ቫይረስ በደቸው ውስጥ የሌለ ቢሆንም የምርመራ ውጤቱ ግን አለ ብሎ አመላክል፡፡ ይህ የተሳሳተ ኤችአይቪ በደሜ ውስጥ አለ ብሎ መግለጽ ነው፡፡
- በተጨማሪ 1.8% የሚሆኑ የጥናቱ ተሳታፊዎች (16 ከ 900) ምንም ዓይነት የምርመራ ውጤት ማግኘት ሳይችሉ ቀርተዋል፡፡




### የኪቱ ይዘቶች

- አንድ ጥቅል ኪት በውስጡ የሚከተሉትን ይይዛል፥
  - የተከፋፈለ ጥቅል (5X4-0004) ከነጠላ መመርመያ፣ ማቆያ እና ፈሳሽ ጋር
  - የመመርመሪያ ማስቀመጫ
  - የአጠቃቀም መመሪያዎች

አስፈላጊ መሳርያዎች ነገር ግን በጥቅሉ ውስጥ ያልተካተቱ ፥ ሰአት፣ የእጅ ሰአት ወይም የሰአት መቆጣጠርያ ናቸው፡፡

### ⚠ ማስጠንቀቂያና ቅድመ-ጥንቃቄዎች

- አብዛኛዎቹ ሰዎች የኤች አይ ቪ ምርመራ በሚወስዱበት ጊዜ ትንሽ ፍርሃት ይሰማቸዋል። ነገር ግን ምርመራውን ለማድረግ በጣም ፍርሀት ከተሰማዎት፣ እስኪረጋጉ ይጠብቁ ወይም በሀኪሞ ወይም በአካባቢዎ ባለ ክሊኒክ ሄደው መሞከር ይችላሉ።
- ኤች አይ ቪ በደሞ ውስጥ እንዳለ የሚያውቁ ከሆነ ምርመራውን አያድርጉ፡፡
- ለምርመራው የአፍ ፈሳሾችን ብቻ ይጠቀሙ። ምርመራውን ከደም፣ ከጡት ወተት፣ ከፕላዝማ፣ ከዘር ፈሳሽ፣ ከሽንት፣ ከሴት ብልት ፈሳሽ ወይም ላብ በሚወሰድ ናሙና አይደረግም።
- ምርመራውን ከመጀመርዎ በፊት ቢያንስ ለ15 ደቂቃዎች ምግብ ወይም መጠጥ አይውሰዱ።
- ምርመራውን ከመጀሮ ከ30 ደቂቃ በፊት የአፍ ጽዳት መሳሪያዎችን አይጠቀሙ።
- የአፍ ፈሳሽ ናሙና ከመውሰዶ በፊት ድድዎትን የሚሸፍኑ የጥርስ ምርቶችን እና ሌሎች ሰው ሰራሽ ነገሮችን ያስወግዱ።
- ከጥቅሉ ውስጥ የጠፋ፣ የጎደለ፡ የተሰበረ ወይም የተከፈተ ከሆነ ፤ ይህንን መመርመሪያ አይጠቀሙ።
- ጥቅሉ ላይ ያለው የምርት የአገልግሎት ዘመን ካለቀ ይህንን ምርመራ አይጠቀሙ።
- የምርመራ ውጤትን ለማንበብ የሚያስችል በቂ ብርሃን ሊኖር ይገባል። በምርመራ መሳሪያው የ "T" እና "C" ምልክት በተደረገባቸው ቦታዎች ላይ ሁለት መስመሮች ከተገኙ የምርመራ ውጤቱ ኤች አይ ቪ በደሞ ውስጥ አለ ተብሎ ይተረጎማል።
- ምርመራውን ለማድረግ ዝግጁ ካልሆኑ መመርመሪያውን አይክፈቱ።
- ለቤት ውስጥ የማጽጃ ቁሶች (ለምሳሌ, በረኪና) ከተጋለጡ ምርመራው አያድርጉ።
- የኤች አይ ቪ ክትባት ክትትል የሚደረግበት ክሊኒካዊ ጥናት ውስጥ ከተሳተፉ፣ ይህ ምርመራ የተሳሳተ ተ ውጤቱ ሊያሳይ ይችላል፡፡ ነገር ግን በ ኤች አይ ቪ ተይዘዋል ማለት ላይሆን ይችላል። በቅርቦ ካለ የጤና ተቋም ጋር መከታተል ይገባዎታል።
- ዕድሜዎ 11 ወይም ከዚያ በታች ከሆነ ይህንን ምርመራ እንዲጠቀሙ አይመከርም፡፡

30 °C **ማከማቻ**
2 °C

- የመመርመሪያ መሳሪያውን በቀዝቃዛ አካባቢ ያስቀምጡ ወይም ያከማቹ፡፡
- መመርመሪያው ከ2°-30° C (36°-86° F) ውጪ ተከማችቶ ከነበረ ለምርመራ አይጠቀሙት።
- ይህንን ምርመራ በ15°-37° C (59°-99° F) ባለ ሙቀት ውስጥ መከናወን ይኖርቦታል።

### የምርመራው ገደቦች

- ትክክለኝ ውጤት ለማግኘት ይህንን OraQuick® ኤች አይ ቪ ራስን በራስ መመርመሪያ የአጠቃቀም መመሪያዎች በጥንቃቄ መከተል አለቦት።
- የፀረ ኤች አይ ቪ ህክምና የሚከታተሉ ከሆነ የተሳሳተ ውጤት ሊያገኙ ይችላሉ።
- የ HBV፣ HCV ወይም HTLV (I/II) ካለቦት፣ የተሳሳተ ውጤት ሊያገኙ ይችላሉ።
- የአፍ ውስጥ ደም መፍሰስ ልክ ያልሆነ ውጤት ሊያስከትል ይችላል። የምርመራው ውጤት የተሳሳተ ከሆነ፣ በአቅራቢያዎ የሚገኘውን የጤና ተቋምን ይጎብኙ።
- የኤችአይቪ መከላከያ PrEP እየተጠቀሙ የሚገኙ ግለሰዎች የOraQuick® የራስ ፍተሻ ለማሳየት የሚያስችል ክሊኒካዊ መረጃዎች አልተሰበሰበም።
- የ OraQuick® የኤች አይ ቪ ራስ መመርመሪያ ባለፉት 3 ወራቶች ውስጠ የተፈጠረ ኤች አይ ቪን ላያሳይ ይችላል።
- ኤች አይ ቪ በደሞ ውስጥ መኖሩን የሚያሳይ ውጤት፣ የምርመራው ድመቀት የፀረ ተዋሳህያን መጠን አያሳይም።
- የኤች አይ ቪ ምርመራ ውጤቶን በሰለጠነ ባለሙያ ሌላ ምርመራ በመድረግ ማረጋገጥ አለቦት።

### ጥያቄዎችና ምላሾች

1. ***ምርመራው ምን ይሰራል?***
   OraQuick® የ ኤች አይ ቪ ራስ መመርመሪያ በአፍ ፈሳሾች የሚደረግ የኤችአይቪ (HIV-1 እና HIV-2) ራስን በራስ በመመርመር መመርመር የሚከናወን ነው፡፡ ይህ ምርመራ ተፈጥሮአዊ ፀረ ተዋሳህያን አካላትን በመለየት ይሰራል። ኤች አይ ቪ አለ የሚል ዉጤት ከተገኘ ተጨማሪ ምርመራ በህክምና ተቋም ማድረግ ይኖርቦታል።
2. ***ኤች አይ ቪ የሚያጋልጡ ክስተቶች ምድን ናቸው?***
   - ከተለያዩ የጾታ አጋሮች ጋር ወሲብ መፈፀም
   - ከኤች አይ ቪ ጋር ከሚኖር ሰው ጋር ወሲብ መፈጸም
   - ህገ ወጥ የሆኑ የሚወጉ መድሃኒቶችን ወይም ስቴሮይድ በመጠቀም
   - ምላጮች ወይም መርፌዎች መጋራት
   - ለገንዘብ ብሎ ወሲብ መፈፀም
   - ለጉበት ህመም፣ ለሳንባ ነቀርሳ ወይም ለአባላዘር በሽታዎች ከዚህ በፊት ተጋልጠው ወይም ታክመው ከነበረ
3. ***ከተጠቀሱት ለኤችአይቪ የሚያጋልጡ ክስተቶች አንዱን ካደረኩ በኋላ እራሴን ለመመርመር ምን ያህል ጊዜ መጠበቅ ይኖርብኛል?***
   በማንኛውንም ጊዜ መመርመር ይችላሉ ነገር ግን ይህ ምርመራ ለኤችአይቪ የሚያጋልጡ ክስተቶችን ካደረጉበት ጊዜ ከ 3 ወራት በፊት ከተጠቀሙ እና የምርመራ ውጤቱ ኤች አይ ቪ በደሞ የለሌ መሆኑን ከጠቆመ፣ ውጤቶ ምናልባት ትክክል ላይሆን ይችላል። እርግጠኛ ለመሆን ለኤችአይቪ የሚያጋልጡ ክስተቶችን ካደረጉበት ከ3 ወራት በኋላ እንደገና መመርመር ይኖርቦታል። በተጨማሪም በጤና ተቋም በመሄድ መመርመረ ይችላሉ።
4. ***ለምንድነው ለኤችአይቪ ሊያጋልጥ የሚችለውን ድርጊት እንደፈፀምኩ ይህንን ምርምራ የማላደርገው?***
   በቫይረሱ ከተያዙ ሰውነትዎ ተፈጥሮአዊ ጸረ ተዋሳህያንን በማምረት የኤች አይ ቪ ቫይረሱን ለመዋጋት ይሞክራል። እነዚህ ጸረ ተዋህሳያን አካላት በአፍ ፈሳሽዎ ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ። ነገር ግን ሰውነትዎ እነዚህን ጸረ ተዋህሳያን አካላት እንዲፈጠሩ እና በዚህ ምርመራ ሊታዩ በሚችሉት ደረጃ ላይ እስኪደርሱ እስከ 3 ወራት ጊዜ ይወስዳል።
5. ***ምርመራው ምን ያህል ትክክለኛ ነው?***
   ጥናቶች እንደሚያሳዩት በደማቸው ውስጥ ኤችአይቪ ቫይረስ ይኑርባቸው አይኑርባቸው የማያውቁ 900 ሰዎች ኤችአይቪን ራስን በራስ መመርመርያ OraQuick® እራሳቸውን በራሳቸው እንዲመረምሩ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ውጤቱም በላቦራቶሪ ውስጥ ከሚገኝ የ4ተኛ ትውልድ የኤች አይ ቪ መመርመሪያ ጋር እንዲነፃፀሩ ተደርጓል፡፡ የላብራቶሪ ውጤቱ እንደሚያሳየው 153 ሰዎች ኤችአይቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ የተገኘ ሲሆን 724 የሚሆኑት ደግሞ አልተገኘባቸውም፡፡ ሰባት (7) ሰዎች ከጥናቱ እንዲወጡ ተደርጓል፡፡ የውጤቶቹ ንጽጽር ከዚህ እንደሚከተለው ነው፥
   - 99.4% የሚሆኑት ሰዎች (ከ153 ውስጥ 152) ውጤታቸው ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ እንዳለ የሚያሳይ መሆኑን በትክክል ገልፀዋል፡፡ ይህ ማለት ከ153 ሰዎች ውስጥ 1 ሰው ኤች አይቪ ቫይረስ በደሙ ውስጥ እያለ የለም ብሎ ገልጻል ማለት ነው፡፡
   - 99.0% የሚሆኑት ሰዎች ማለትም ከ (717/724) ውጤታቸው ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ እንደሌለ በትክክል ገልፀዋል፡፡ ይህም ማለት ከ724 ሰዎች ውስጥ 7 ሰዎች ኤችአይቪ ቫይረስ በደቸው ውስጥ የሌለ ቢሆንም የምርመራ ውጤቱ ግን አለ ብሎ አመላክል፡፡ ይህ የተሳሳተ ኤችአይቪ በደሜ ውስጥ አለ ብሎ መግለጽ ነው፡፡
   - በተጨማሪ 1.8% የሚሆኑ የጥናቱ ተሳታፊዎች (16 ከ 900) ምንም ዓይነት የምርመራ ውጤት ማግኘት ሳይችሉ ቀርተዋል፡፡
6. ***ይህንን ምርመራ በመጠቀሜ ኤች አይ ቪ ሊይዘኝ ይችላልን?***
   ይህንን ምርመራ በመጠቀሞ የኤች አይ ቪ ቫይረስ በፍጹም ሊይዞ አይችልም።
7. ***የኤች አይ ቪ ምርመራ በምን ያህል ጊዜ መደረግ ይኖርበታል?***
   እስከ አሁን የኤች አይ ቪ ምርመራ ፈጽመው ካላደረጉ ቢያንስ አንድ ጊዜ ምርመራ ማድረግ ይኖርቦታል። ለኤች አይ ቪ ሊያጋልጥ የሚችል ድርጊት ፈጽመው ሲገኙ ደግሞ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መመርመር ይኖርቦታል (የዓለም የጤና ድርጅት ምክሮች)።
   **ለኤች አይ ቪ ሊጋለጡ የሚችሉበት ክስተት ከፍተኛ ሆኖ ከተሰማዎት በየጊዜው መመርመር ይኖርቦታል።**
8. ***ከኤች አይ ቪ ነጻ ውጤት ማለት ምን ማለት ነው?***
   ከኤች አይ ቪ ነጻ ውጤት ማለት ምርመራው ምንም ዓይነት የጸረ ተዋህሳያን አካላት አላሳየም ማለት ነው። ሆኖም ግን ምርመራው ኤች አይ ቪን በትክክል ለመለየት እንዲያስችል ከተጋላጭነት ከተከሰተ 3 ወር ጊዜ በኋላ መደረግ ይኖርበታል። ለቫይረሱ ሊያጋልጥ የሚችል ክስተት ካጋጠሞት ቢያንስ 3 ወራት በኋላምርመራው ከተከናወነ እና በጥንቃቄ መመሪያውን ከተከተሉ፣ ውጤቱ ትክክል ይሆናል። የተጋላጭነት ክስተቱ ካጋጠሞት ከ3 ወራት ያነሰ ከሆነ፣ ለመመርመር ሙሉዉን 3 ወራት ይጠብቁ ወይም ወደ ጤና ተቋም ይሂዱ።
9. ***ከኤች አይ ቪ ነጻ መሆኔን ካረጋገጥኩ ምን ማድረግ አለብኝ?***
   በነዚህ ያለፉ 3 ወራት ምንም የተጋላጭነት ስጋት የተጋላጭነት ስጋት ካላጋጠምዎት፣ እና በጥንቃቄ መመሪያውን ተከትለው ምርመራውን ካከናወኑ፣ እርግጥም ቫይረሱ በደሞው ውስጥ የለም ማለት ነው፡ ፡ ነገር ግን መመሪያዎችን በጥንቃቄ ካልተከተሉ፣ ውጤቱ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ድጋሚ መመርመር ይኖርቦታል። ባለፉት 3 ወራትጊዜ ውስጥ ማንኛው ለቫይረሱ ሊያጋልጥ የሚችል ስጋት ቢኖርዎ፣ የምርመራው ውጤቱ የተሟላ ላይሆን ይችላል፡፡ ምርመራው መለየት በማይቻልበት የጊዜ ገደብ ውስጥ አንድ ሰው በኤች አይ ቪ ከተያዘ እስከ አሁን ድረስ ሰውነታቸው ጸረ ተዋህሳያንን አላመረተም ማለት ነው። ባለፉት 3 ወራት ውስጥ ለኤች አይ ቪ የተጋለጡ ከመሰለዎት ፤ ከ3 ወራት በኋላ እንደገና መመርመር የኖርቦታል። ለኤች አይ ቪ ሊያጋልጡ የሚችሉ አደጋዎች ውስጥ መሳተፎን ከቀጠሉ በየጊዜው መመርመር ይኖርቦታል።
10. ***ኤች አይ ቪ በደሞ ውስጥ አለ የሚል ውጤት ማለት ምን ማለት ነው?***
    ኤች አይ ቪ በደሞ ውስጥ አለ የሚል ውጤት ማለት ኤች አይ ቪ ለኖርብዎ ይችላል ማለት ነው። ውጤቱን ለማረጋገጥ በአካባቢዎ ወደሚገኝ ጤና ተቋም ሄደው ተጨማሪ ምርመራ ማደረግ ይኖርቦታል።
11. ***ኤች አይ ቪ በደሜ ውስጥ አለ የሚል ውጤት ካገኙሁ ምን ማድረግ አለብኝ?***
    ውጤቱን ለማረጋገጥ ከጤና ተቋማት ጋር ተጨማሪ ምርመራ ማድረግ ያስፈልግዎታል። በዚያን ጊዜ ከሀኪሞ ወይም የጤና እንክብካቤ ባለሙያ ጋር መወሰድ ያለባቸውን ቀጣይ እርምጃዎች ይወያያሉ።
12. ***በዚህ ምርመራ ትክክል ያልሆነ ወይም የተሳሳተ ከኤችአይቪ ነጻ ውጤት ማግኘት እችላለሁ?***
    ትክክል ያልሆነ ወይም የተሳሳተ ከኤች አይ ቪ ነፃ ውጤት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊከሰት ይችላል፥
    - ምርመራውን ከማድረጎ በፊት ከ3 ወር ያነሰ የተጋላጨነት ክስተት ካለብዎት
    - የአጠቃቀም መመሪያዎችን በጥንቃቄ ካልተከተሉ
    - የአፍ ፈሳሽ ማጠራቀሚያ ውስጥ ተፈጥሯዊ ድድዎትን የሚሸፍኑ የጥርስ ምርቶች ወይም ሌሎች ምርቶችን ከተጠቀሙ
    - በአፍ የሚወሰድ የኤችአይቪ መከላከያ ኤችአይቪ መከላከያ PrEP ወይም ፀረ ኤች አይ ቪ ህክምና (ARV) ላይ ከሆኑ።
13. ***በዚህ ምርመራ ላይ የተሳሳተ ኤች አይ ቪ በደሜ ውስጥ አለ የሚል ውጤት ላገኝ እችል ይሆን?***
    ትክክል ያልሆነ ኤች አይ ቪ በደሞ ውስጥ አለ የሚል ውጤት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊከሰት ይችላል፥
    - የተሳሳተ የምርመራ ውጤት እንዳለ አድርጎ በማንበብ
    - የአጠቃቀም መመሪያዎችን በጥብቅ ካልተከተሉ
    - ምርመራ ከማድረጎዎ በፊት ተመግበው፣ ጠጥተው ለ15 ደቂቃዎች ባለመጠበቅዎ ወይም ምርመራ ከማድረገዎ በፊት የአፍ ንጽህና ምርቶችን ተጠቅመው ለ30 ደቂቃዎች ባለመጠብቅዎ ምክንያት
    - የኤች አይ ቪ ክትባት ከወሰዱ
    - ድድን በተደጋጋሚ በመመርመሪያ መሳሪያው ጠርገው ከሆነ
14. ***ስለኤች አይ ቪ ተጨማሪ እርዳታ ወይም ህክምና የት ማግኘት እችላለሁ?***
    በአካባቢዎ ካለ የጤና ተቋም ከሚገኝ የህክምና ባለሙያ ወይም የጤና እንክብካቤ ባለሙያ ተጨማሪ እርዳታ ማግኘት ይችላሉ።
15. ***ኤች አይ ቪን ለመከላከል የሚያግዘውን ክኒን (oral PrEP) እየወሰድኩ ይህንን ምርመራ ማድረግ እችላለሁ?***
    ለኤች አይቪ መከላከያ የሚያገለግለውን ክኒን (oral PrEP) እወስዱ ከሆነ የተሳሳተ ውጤት ሊያገኙ ይችላሉ።
16. ***ምርመራዬ በትክክል እየሰራ መሆኑን እንዴት ማወቅ እችላለሁ?***
    ምርመራው በትክክል እየሰራ ከሆነ መመርመሪያ መሳሪያዎ ላይ ካለው "C" ቀጥሎ መስመር ያያሉ። ከ "C" ቀጥሎ መስመር ከሌለ ምርመራዎ አልሰራም ማለት ነው።
17. ***ነፍሰ ጡር ከሆንኩ ይህን ምርመራ መጠቀም እችላለሁ?***
    አዎ ነፍሰ ጡር ሆነው ይህን ምርመራ በማነኛውም ጊዜ መጠቀም ይችላሉ፡፡

### ውጤቱን ሊቀይሩ የሚችሉ ንጥረነገሮች እና የጤና ሁኔታዎች

ጥናቶች እንደሚያሳዩት የተሳታፊዎቹ ተጓዳኝ በሽታዎች ወይም የጤና እክሎች፣ የአፍ በሽታዎች፣ የኤችአይቪ ያልሆኑ የቫይረስ ኢንፌክሽኖች ፤ እና በሌሎችም ምክንያቶች (ለምሳሌ፣ የትንባሆ ምርትን መጠቀም፣ በምርመራው በ24 ሰአት ውስጥ አፍን ማጽዳት፣ ተዛማችነት መድሀኒቶች፣ የጥርስ ህክምናዎች፣ እንዲሁም ምግብ እና መጠጥ ወዲያውኑ ምርመራ ከማድረግዎ በፊት) መረጃ ተሰብስቧል። በተለየ የ40 ግለሰቦች ጥናት፣ የአልኮሆል ፍጆታ፣ ጥርስ መቦረሽ፣ ምርመራው ከመጀመሩ ከ5 ደቂቃዎች በፊት የአፍ ማጽጃ ወይም ትንባሆ መጠቀም በምርመራው ምንም ተጽእኖ አላሳየም። የHBV፣ HCV ወይም HTLV (I/II) በሽታዎች ካሉ፣የተሳሳተ ውጤት ሊያገኙ ይችላሉ። ተጠቃሚዎች ምግብ እና መጠጥ ከወሰዱ በኋላ ለ15 ደቂቃዎች ያህል እና የአፍ እንክብካቤ ምርቶች ከተጠቀሙ በኋላ ለ30 ደቂቃዎች ያህል እንዲጠብቁ ይመከራሉ።

## የምልክቶች ማብራሪያ

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| LOT | የምርት ክምችት ምልክት | REF | የካታሎግ ቁጥር | ⚠ | የጥንቃቄ እና ምክር ተጓዳኝ ሰነዶች | ℹ | የአጠቃቀም መመሪያዎችን በጥንቃቄ ያንብቡ |
| ⊘ | እንደገና አይጠቀሙ | IVD | የምርመራ ህክምና መሳሪያ | | አምራች | EXP | አገልግሎት ዘመን ማብቂያ ቀን |
| | የሙቀት መጠን ገደብ | ⌛ | ተጠቃሚዎች | | | DOM | የተመረተበት ቀን |

በታይላንድ የተመረተ


OraSure Technologies, Inc.
220 East First Street,
Bethlehem, PA 18015 USA
(+1) 610-882-1820
www.OraSure.com



© 2016, 2018 OraSure Technologies, Inc. • OraQuick®፣ የሎጎ ቅርጽ እና ውቅረት OraSure Technologies, Inc. የንግድምልክቶች ናቸው።



ንጥል ነገር #3001-3010 rev. 01/18B